ሳምንታዊ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ
የካቲት 7 ቀን 2001 ዓ.ም.

- መለስ የተለመደ የበሬ ወለድ ጋዜጣዊ መግለጫዉን ሰጠ፤

- የመንግስት ሠራተኞችን የማባረር ዘመቻ ወደ መምህራኖች ሊሸጋገር መሆኑ ተነገረ፤

- የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት ርዕስ መምህራኖች ለቀበሌና ለዞን ካድሬነት ተመርጠዉ ሄዱ በምትካቸዉ ካድሬዎች በቦታቸዉ ተቀመጡ፤

- 69 የእሳት አደጋ ማጥፊና መከላከል ሰራኞች ከስራ ተባረሩ፤

የሚሉና ሌሎቹም ይገኙበታል፡፡ ዝርዝሩን ከሚቀጥለዉ ገፅ ጀምረዉ ያንብቡ »»»

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ አርብ የካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም. ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ጋዜጠኞች ድንገተኛ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ።በዚሁ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ዛሬም ያልተጨበጠና ምንም በሌለ ነገር ላይ ሲወተውትና ሲቀጥፍ መዋሉ ታውቆዋል።

በአሁኑ ወቅት በአለም ላይ ስለተከሰተው የኢኮኖሚ እና የገንዘብ ቀውስ ዙሪያ ሀገሪቱ የደረሰባት ተጨባጭ ችግር እንዴት ይገለፃል ? ተብሎ ለተጠየቀው ሲመልስ በወያኔ አመራር ሰጭነት ችግሩ ሊቀረፍ እንደቻለና ምንም የሚያሰጋ ነገር እንዳልተፈጠረ ገልፆ ወደ ፊትም በያዙት መንገድ እንደሚቀጥሉበት ገልፆዋል።

በአሁኑ ሰዓት በመላው ዓለም ላይ የአንድ ድፍድፍ ነዳጅ ዋጋ በሚያስገርም ሁኔታ ዋጋው አሽቆልቁሎ ከ40 ዶላር በታች እየተሸጠ በእኛ ሀገር ግን ቀድሞ ከነበረው ብዙም ለውጥ ሳያሳይ በሊትር 8 ብር እየተሸጠ መሆኑን ገልፀዋል።

በአፍሪካ ውስጥ ያሉት ነባርና ልምድ ያካበቱ ባንኮችን የመንደር ባንኮች ናቸው እያለ ሲዘረጥጣቸው የዋለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የአለም የገንዘብ ቀውስ ያልደረሰባቸው ብዙ እንቅስቃሴ ስለማያደርጉ ነው ሲልም አስገራሚ መግለጫ ሰጥቶዋል።

በሀገር ውስጥ ያለው የግብርና ምርቶቻችን በየዓመቱ እያደገ ነው ። በዓለም ላይ የተፈጠረውን የኢኮኖሚ ቀውስ ልንቋቋቁዋመው ችለናል ያለው መለስ በተለይ የዘንድሮውን መንገድ ተጠቅመን በሚቀጥለውም ዓመት ተግባራዊ ካደረግን ያለምንም ስጋት ልንወጣው እንችላለን በማለት ምላሽ የሰጠው መለስ ዜናዊ የሀገር ውስጥ ገንዘብ ትርጉም አልባ ሆኖ ዋጋ አጥቶ  የአንድ ኩንታል ጤፍ ቀድሞ 300 ብር ሲሸጥ የነበረው ዛሬ 1300 ብር ፣የአንድ ኪሎ ስኩዋር ዋጋ 5 ብር የነበረው ዛሬ 14 ብር ሆኖ ባለበት ፤ የሽቀጣሽቀጥ ፤ የጥራጥሬ ዋጋ አሻቅቦ በናረበት በዚህ ወቅት የአንድ ዶላር ዋጋ ከ9 ብር ወደ 11 ብር ከ25 ሳንቲም በዘለለበት እና ገንዘቡ የመግዛት አቅሙ በተዳከመበት ወቅት ይህን የመሰለ ማን አለብኝነት የተጠናወተው ምላሽ መስጠቱ በእጅጉ እንደዜጋ አንገት የሚያስደፋ ነው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ሲገልፁ ተደምጠዋል።

ወያኔ የውጭ ምንዛሪ በማጣቱ የተነሳ በአስመጪና ላኪዎች ላይ ከፍተኛ እንቅፋት እንዲሁም በፋብሪካዎችና በሌሎችም የንግድ ተቋዋሞች ላይ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮ ብዙ ድርጅቶች ስራ እስከማቆምና ሰራተኞቻቸውን እስከ ማባረር ድረስ ተደርሶ ባለበት ወቅት ከዚህ ቀደም ሲያወግዘውና ሲያጣጥላው የነበረውን ፍራንኮ ቫሉታ የተባለውን የገንዘብ ዝውውር በሚስጢር መጀመሩ ታውቆዋል።

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በ1988 ዓ. ም. ሲሰራበት የነበረውን ይኸው ፍራንኮ ቫሉታ በህግ ደንግጎ ያስቀረ መሆኑን እና ወንጀል እንደሆነ ቢለፍፍም ዛሬ የውጭ ምንዛሪ በማጣቱና በመቸገሩ ምክንያት ከባንክ ነጻ በሆነ ሁኔታ ነጋዴዎች በራሳቸው መንገድ እቃ እንዲያስመጡ ሳይወድ በግድ በምስጢር መፍቀዱ ታውቆዋል።

በሀገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ ምህዳር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበበ መሄዱን የሚያሳዩ ምልክቶች እየታዩ ነው በሰላማዊ መንገድ እንታገላለን የሚሉ የፓርቲ መሪዎች እየታሰሩ ነው ቢሮዋቸውም እየተዘጋና አባሎቻቸው ላይ ችግር እየደረሰባቸው ነው እየተባለ ወቀሳ እየተሰነዘረባችሁ ነው ።ለዚህስ ምን ምላሽ አለዎት ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ እንዲህ ያለ ስሞታ የሚያናፍሱት የእኛን መውደቅ የሚናፍቁ ተስፈኞች ወሬ እንጂ እኛ አቅም በፈቀደ መጠን ተቻችሎ እና ተደጋግፎ ለመሔድ ጥረት እያደረግን ነው

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ከኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በዘረፈችው ሀብት የተለያዩ ግዙፍ ድርጅቶችን አቋቋቁማ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርታ እንደምትገኝ ምንጮች አጋለጡ።

እንደ ምንጮቹ ገለፃ ከሆነ አዜብ መስፍን በተለያዩ የንግድ ስራ ላይ መሰማራት የጀመረችው የህወሀት ክፍፍል ከተፈጠረ በሁዋላ መሆኑን ገልፀው በተለይ ከክፍፍሉ ወዲህ ያለ ምንም ይሉኝታና ሀፍረት በአጭር ጊዜ ቢሊየነር ለመሆን የበቃች መሆኑን አስረድተዋል።

በኮንስትራክሽን ስራ ላይ ከ40 በላይ አዳዲስ ገልባጭ ኒሳን ዲዝል መኪኖችን አሰማርታ በስራ ላይ ስትሆን በመኪና አስመጪነት እና ሻጭነት እንዲሁ ካሉት ነጋዴዎች በበለጠ እየሰራች መሆኑንም ጨምረው አስረድተዋል። የወያኔው መሪ መለስ ሚስት አዜብ መስፍን ፊደል ባልቆጠሩ ከገጠር ባስመጣቻቸው የቅርብና የሩቅ ዘመዶችዋ ስም እንዲሁም ከጉራጌ ብሔር ተወላጅ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር ከፍተኛ የንግድ ተቋዋማትን ከፍታ እየሰራች መሆኑን አጋልጠዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የእለት ጉርሱን ተቸግሮ ባለበት በዚህ ወቅት ከሀገር እና ከህዝብ ላይ ከባለቤቱዋ ጋር በዘረፉት ገንዘብ ግዙፍ ድርጅቶችን በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ከፍተው ከመንቀሳቀሳቸው በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ትላልቅ ኩባንያዎችን ከፍተው እያስነገዱ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በተለይ በቡና ስራ ላይ ከተሰማራች አጭር ጊዜ ቢሆንም ከ20 ዓመታት በላይ በቡና ንግድ ላይ ከተሰማሩት ነባር ነጋዴዎች በላይ ከፍተኛ ስራ እየሰራች ከመሆኑም

በተጨማሪ ሌሎች ነጋዴዎች ወደ ውጭ እንዳይልኩና እንደቀድሞዋቸው እንዳይሸጡ የተለያዩ ስውር እንቅፋቶችን እየፈጠረች ለኪሳራ እየዳረገቻቸው መሆኑን እነዚሁ ምንጮች አጋልጠዋል::

ሰሞኑን ደግሞ ስፋት ያለው መሬት በአዲስ አበባ ዙሪያ አለም ገና ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተረክባ አጥር አጥራ ያስቀመጠች መሆኑን የገለፁት ምንጮች አስረድተዋል::

ወያኔ ለስልጣን እድሜዬ ማራዘሚያ ይሆነኛል በሚል በቅርቡ በመላ ሀገሪቱ ባሉ መንግስት ሰራተኞች ላይ አዲስ የስራ ለውጥ እያለ እያመሰ መሆኑ ተዘገበ::

ከጥር 1 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ በተለያዩ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ነባር ሰራተኞችን የማባረር እና የማንሳፈፍ እርምጃ እየወሰደ ሲሆን፤ በተለይ በርካታ ነባር ሰራተኞች ከስራ ውጭ እየሆኑ እንደሆነ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ለብዙ ዓመታት በመምህርነት ስራ ላይ ተሰማርተው ያሉትን ዜጎች በወያኔ የወረዳ እና የቀበሌ ሹመኛ ካድሬዎች ውስጥ ውስጡን ስለላ እየተደረገባቸው ከማን ጋር ዋለ፤አቋዋሙ ምንድነው፤ ከየትኛው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ነው የወገነው፤ በሚሉና በመሳሰሉት መመዘኛዎች በምስጢር መምህሩ በማያውቀው መንገድ ተገምግሞ ያለቀ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ከዚህም በተጨማሪ በየትምህርት ቤቱ ውስጥ የተመደቡ አዳዲስ አፍለኛ መምህራንን ብቁ ማድረግ በሚል ሰንካላ ምክንያት በርካታ መምህራን የመባረር እጣ ሊደርስባቸው እንደሚችል ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ተማሪውን ሲያሳድሙ ነበር ተማሪው የመብት ጥያቄ ማንሳት እንዲችል ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ ሲያደርጉ ነበር ተብለው በተለይ በ1997ዓ. ም. እና በ1998 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩት በመምህራን ቀስቃሽነት ነው በሚል ሊያሰናብቱዋቸው ዝግጅቱ መጠናቀቁን የደረሰን ዘገባ አመልክቱዋል::

በቅርቡ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ መምህራኑን ሰብስበው ማስጠንቀቂያ ሲሰጡ የነበሩት የወያኔ ካድሬዎች « በስራችሁ ላይ መቀጠል ከፈለጋችሁ መጀመሪያ እንደ ንስር አሞራ ጥፍራችሁን ነቅላችሁ ሌላ ማብቀል ይጠበቅባችሁዋል» እያሉ የወያኔ አባል መሆን ግዴታ እንደሆነ ሲያስፈራሩዋቸው የነበረ ቢሆንም ከተሰብሳቢ መምህራኖች መሀከል ስብሰባውን ጥለው የወጡ እንደነበሩ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

ወያኔ የፖለቲካ እንቅስቃሴውን በተለይ በቀበሌ ደረጃ ይመሩልኛል በሚል ከየትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህራኖችን የፖለቲካ ፀበል እያጠመቀ በካድነት እየመደባቸው ሲሆን ሲሆን ለየትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርነት ደግሞ ቀድሞ ቀበሌና ወረዳ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩትን ካድሬዎች በምትካቸው እየመደበ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ርዕሰ መምህር ሆነው የሚመደቡት የወያኔ ካድሬዎች ስለ ትምህርት አንዳችም እውቀቱ የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ ትምህርት ቤቱን የካድሬዎች መፍለቂያ ለማድረግ እና የተማሪዎችን አመፅ እና ተቃውሞ ለመቆጣጠር ሆን ተብሎ ታቅዶና ታልሞ የተሰራ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ ከዚህ በተጨማሪም መምህራኑን መልምለው አባል ለማድረግም በስፋት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ መመሪያና ትዕዛዝ ከነ በረከት ስምኦን እንደተሰጣቸውም ገልፆዋል።

ወያኔ ለአገዛዜ ይመቹኛል ያላቸውን ስራ እየመደበ የሚጎረበብጡኝ ናቸው ያላቸውን ደግሞ በቅርቡ በጀመረው አዲስ የሰውራ ለውጥ የሚል ሰንካላ ምክንያት በተለያዩ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ምንጠራ እያደረገ መሆኑ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የሚደርሰን ዘገባ ገለፀ።

ቀድሞ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ስር ሲንቀሳቀስ የነበረው የአዲስ አበባ እሳት ማጥፊያና መከላከል ነባር ሰራተኞችን ሰሞኑን ባደረገው የማባረር ዘመቻ 69 ያህሉ የዚሁ ገፈት ቀማሾች ሲሆኑ ዘመቻው ቀጣይ እንደሆነም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

እነዚሁ የአዲስ አበባ እሳት ማጥፊያ እና መከላከል ሰተራተኞች ከ20 ዓመት እና ከዛም በላይ ያገለገሉ ቢሆንም ወያኔ የአይናችሁ ቀለም አላማረኝም በሚል ከስራ ያባረራቸው ከመሆኑም በላይ ጠዋት ጠዋት በየቀኑ የሰዓት ፊርማ እንዲፈርሙ ትዕዛዝ እንደተሰጣቸው ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል።

የወያኔ ካድሬ ኩማ ደመቅሳ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ከተሾመ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ነባር እና እውቀት ያላቸውን ሰራተኞች እያባረረ ልምድ እና እውቀት የሌላቸውን የወያኔ ተለጣፊ ሆነው የተመለመሉ ወጣቶችን እየሰገሰገ መሆኑን በተለይ በአዲስ አበባ ምክር ቤት የመምሪያ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ የነበሩትን ቀስ በቀስ እያባረረ መሆኑን ዘገባ አብራርቶዋል።

ወያኔ አዲስ የስራ ለውጥ በሚል የጀመረው ነባር ሰራተኞችን የማባረር ዘመቻ በሁሉም መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚቀጥል መሆኑንም ይኸው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።